የአማራ ሚዲያ ካውንስል
AMHARA MEDIA COUNCIL

ግንቦት 1 ቀን 2017 ዓ/ም

**የአማራ ፋኖ ብሔራዊ ኃይል መመስረቱን ተከትሎ ከዐማራ ሚዲያ ካውንስል የተሰጠ የደስታና የድጋፍ መግለጫ!**

የዐማራ ሚዲያ ካውንስል በዛሬው እለት ይፋ ለሆነው የዐማራ ፋኖ ብሄራዊ ሃይል ሙሉ ድጋፉን ይገልጻል።

የአማራ ሕዝብ የገጠመውን የህልውና አደጋ ለመቀልበስ ባለፉት 22 ወራት የአማራ የቁርጥ ቀን ልጅ ፋኖ በበርካታ አስደናቂ ተጋድሎ፣ መስዋዕትነት እና ጀብዱዎች ለዛሬዋ ዕለት ደርሷል። ይች ዕለት ለአማራ ሕዝብ ታሪካዊ ዕለትም ሁና ተመዝግባለች። ይህ እንዲሆን በጎ አስተዋጽዖ ላበረከታችሁ ሁሉ የአማራ ሚዲያ ካውንስል አክብሮቱን መግለጽ ይፈልጋል።

የአማራ ፋኖ በአንድ በኩል የአገዛዙን አከርካሪ እየሰበረ በሌላ በኩል የትግሉ እድገት የደረሰበትን የእድገት ደረጃ የሚመጥን አደረጃጀት ይዞ እንዲመጣ በተለይ የትግሉ ባለቤት ከሆነው የአማራ ህዝብ: ከትግሉ ደጋፊ ኢትዮጵያዊያንና እና ከአለማቀፉ ማህበረሰብም ጭምር ከፍተኛ ጥያቄ የነበረ መሆኑ ይታወሳል:: የአማራ የሚዲያ ካውንስልም እንደ አንድ የትግሉ ባለድርሻ የአማራ የሚዲያ አውታሮችን በማስተባበር ቀደም ብሎም እንዲሁም ባለፉት 52 ቀናት "ዘመቻ አንድነት" ግቡን እንዲመታ ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል:: በመጨረሻም የአማራ ህዝብ ታሪካዊ ጥያቄና ምላሽ አግኝቶ ለበርካታ ቀናት በቋራ ታሪካዊ ስፍራ ላይ ጉባኤ ተቀምጠው የነበሩት የአማራ የፋኖ ሃይሎች በዛሬው ዕለት ለዐማራ ሕዝብ ታላቅ የምስራች አሰምተዋል። በእሳት ተፈትኖ እንደብረት ነጥሮ የወጣ አንድ ወጥ የሆነ የአማራን ብሔራዊ ትግል የሚመጥን የአማራ ፋኖን ብሔራዊ ሀይል  መስርተዋል።

ይህ የቋራ ጉባኤ እጅግ ከፍተኛ መስዋእትነት የተከፈለበትና ገና ከጅምሩ ጉባዔው እንዳይሰምር የዐማራን ካለጠፉን እንቅልፍ አይወስደንም ያሉ በርካታ ጸረ-አማራ ሀይሎች ከፍተኛ ርብርብ ያደረጉበትና የአማራን ህዝብ አንገት ለማስደፋት ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም።  ሆኖም እንደሁልግዜው የነዚህ ጠላቶች ውጥን ከሽፎ በአንጻሩ የአማራን ህዝብ አንገት ቀና ያደረገ የብስራት ዜና ከቋራ ተሰማ::  የቋራው ስምምነት ጠላት የጠበቀው ባለመሆኑ በጠላት ዘንድ ከፍተኛ ድንጋጤን ፈጥሯል::

ጠላት የአማራን ህዝብ አንድነት ለመናድ ያስችለኛል ያለውን ወጥመድ ዘርግቶ ቢያደባም የአማራ ፋኖ በብልሃትና በከፍተኛ ጥበብ የወሰናቸው ውሳኔዎች የአማራ ህዝብ ትግል ስልት የደረሰበትን ፖለቲካዊ ከፍታ ያሳየ እንደሆነ ኮውንስላችን ያምናል:: በመሆኑም የአማራ ፋኖ ብሔራዊ ሀይል ለህዝብ ይፋ ያደረገው አደረጃጀት በአማራ ህዝብ ላይ የተደቀነውን የህልውና አደጋ ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ህዝብንና ትግሉን ያስቀደመ እና የጠላትን የሴራ ወጥመድ መና ያስቀረ ልክ እንደ አባቶቻችን ሁሉ ዛሬም ብልሀትና በጥበብ እየተመራን ስለመሆኑ አይነተኛ ማሳያ ሲሆን  የአማራ ሚዲያ ካውንስልም ውሳኔውን በታላቅ አድናቆት የሚመለከት መሆኑንና ዐማራው ለድል እስኪበቃ ድረስ በሚዲያው ዘርፍ የሚሰጠውን ተልዕኮ ለማስፈጸም ከምንግዜውም በላይ ቊርጠኛ መሆኑን ይገልጻል::

የሚዲያ ካውንስሉ ለመላው የአማራ ህዝብ፤ ለመላው የፋኖ አባላትና አመራሮችና ለመላ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በድጋሚ እንኳን ደስ ያላችሁ እያለ በቀጣዩ የትግል ምዕራፍም ከድርጅታችን ከአማራ ፋኖ ብሔራዊ ኃይል ጋር በቆራጥነት በመሰለፍ የሚጠበቅብንን ብቻ ሳይሆን ከሚጠበቅብን በላይ በማድረግ የአማራን ህዝብ ለሁለንተናዊ ድል እንድናበቃ በጋራም ሆነን በቁርጠኝነትና በአርበኝነት መንፈስ እንድንረባረብ ጥሪ እናቀርባለን!

የአማራ ፋኖ ብሔራዊ ኃይል አመራሮችም ይህንን ታሪካዊና ብልሕ ውሳኔ እንዲሁም የአማራን ህዝብ የትግልና የትብብር መንፈስ ይበልጥ በመረዳት ለድርጅታዊ አሠራርና እንደሁልግዜው ሁሉ ለአማራ ህዝብ የህልውና ትግል መስመር ታማኝ በመሆን በጋራ አመራር ይህንን ትግል ለድል እንደምታበቁት እምነታችን የጸና ነው!

በመጨረሻም የአማራ ፋኖ ብሔራዊ ኃይል በዛሬው ዕለት በሰጠው መግለጫ "ለሚዲያ አካላት" በሚል የገለፀውን መልዕክትም ተመልክተናል፣ የተሰጠንን ምክረ ሀሳብም በአክብሮት ዝቅ ብለን ተቀብለናል፣ በተግባርም ወደፊት እናረጋግጣለን።

ድል ለዐማራ ሕዝብ!
የዐማራ ሚዲያ ካውንስል!

Mereja Television
ABC Television
Ethio 251 Media
Roha Media
Ghion Media
Teles Media

MaMa Media
The Amhara Media
Hibir Radio
Black Lion Media
Global Fano Media
Ashara Media